

**በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን።**

# የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶቤተ ክርስቲያን የ2023 ዓመታዊ ሪፖርት

**March, 2024**



በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን።

የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ

ቤተ ክርስቲያን የ2023 ዓመታዊ ሪፖርት

## ሀ.የመንፈሳዊ አገልግሎት ዓመታዊ ሪፖርት

1.በቤተ ክርስቲያናችን ከሰኞ -ዓርብ ዘወትር የኪዳን ጸሎትና የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል
2.በየሳምንቱ ቅዳሜ ጸሎተ ኪዳንና የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል
3.ለልጆች መንፈሳዊ ትምህርት ተሰጥቷል
4.ዲያቆናት ለእሁድ አገልግሎት ጥናት ተደርጓል
5.ቅዳሜ ከሚማሩት ልጆች መካከል አንድ ልጅ የዲቁና ማዕረግ ተቀብሎ አገልግሎት ጀምሮአል
6.ሳምንታዊ የእሁድ አገልግሎት ከ4:00am ጀምሮ ጸሎተ ነግህ ጸሎተ ፍትሐት ጸሎተ ቅዳሴና ስብከተ ወንጌል በልዩ ልዩ መምህራን ተሰጥቷል
7.ምእመናን አገልግሎት በጠየቁት ጊዜ ሁሉ በአካልና በዙም ጭምር አገልግሎት ሰጥቷል

## ለ. የሰንበት ትምሕረት ቤት ዓመታዊ ሪፖርት

1.የቤተ ክርስቲያናችን ሰንበት ተማሪ ወጣቶች በዕለተ ሰንበት ተገኝተው ያጠኑትን መዝሙር በአውደ ምህረት ለምዕመናኑ አቅርበዋል ፤ እንዲሁም በዕለቱ የሚዘመሩትን መዝሙሮች በTV እስክሪን በፖወር ፓይንት አዘጋጅተው አቅርበዋል እንዲሁም በወረቀት አትመው አድለዋል
2.በዓብይት ክብረ በዓላት ተገኝተው አስፈላጊውን የመዝሙር አገልግሎት ሰጥተዋል በተጨማሪም የተለያዩ የፅዳት አገልግሎት የመስተንግዶ አገልግሎት ሰጥተዋል
3.የህፃናቱን ክፍል መዝሙር በማስጠናት ልብስ በማልበስ በአውደ ምህረት እንዲዘምሩ አድርገዋል ፤ በተጨማሪም በየአራተኛው እሁድ መንፈሳዊ ትምህረት ታዳጊ ወጣቶችን አስተምረዋል ፤ እንዲሁም ለደብረ ታቦር እና ለአዲስ ዓመት በተለየ ሁኔታ መዝሙር በመዘመር የገንዘብ ማስገኛ ዝግጅት አድርገው ገቢ አስግኝተዋል
4.የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አስተምረዋል

## ሐ. በጽህፈት ቤት የተከናወኑ እና የተወሰኑ ዋና ዋና ጉድዮች

1.March 5, 2023 ሰበካ ጉባኤ የጠቅላላ ስብሰባ ጠርቶ የ2022 አመት ሪፖርት አቅርቧል
2. የ2023 በጀት ተዘጋጅቶ ለምእመናን ቀርቦ ጸድቋል
3. የቁጥጥር ክፍል አስመርጧል
4. ሪፋይናንስ ለማድረግ ፈቃድ ጠይቆ አስፈቅዷል
5. በመተዳደሪያ ደንባችን አንቀጽ 25 መሰረት የምግባረ ሠናይ (የበጎ አድራጎት)ኮሚቴ እንዲቋቋም ወስኗል
6.በዓላትን በአግባቡ እንድናከብር ሰበካ ጉባኤ አስተባብሯል ፤ በዓላቱም የኪዳነ ምህረት እና የአማኑኤል በዓለ ንግስ እና የመስቀል በዓለ ሲሆኑ በተጨማሪም ዘጠኙንም ዓብይት በዓላትን ፤ብስራት ፤ ልደት ፤ ጥምቀት፤ ደብረ ታቦር፤ ሆሣዕና ፤ ሥቅለት ፤ ትንሣኤ ፤ ዕርገት እና ጰራቅሊጦስ ተከብረዋል
7.ሰበካ ጉባኤው ለቤተ ክርስቲያናችን ገንዘብ የማግኛ መንገድ አቀነባብሮ የሚከተሉት ፈንድ ሬዚይንግ ተደርጓል:

- የአዲስ አመት በዓል (እንቁጣጣሽን) በማክበር ትኬት ተሽጦ ገንዘብ ስብሰባ ተደርጓል
- የኢትዮጵያን ቀን ፕሮግራም ላይ ተሳትፈናል ፤ በፕሮግራሙ ላይ ቁሳቁሶችን በመሸጥ ገንዘብ ተሰብስቧል
- ጊቪንግ ቱዩስዴ በሚባለው የገንዘብ አሰባሰብ ዓመታዊ ፕሮግራም ላይ ተሳትፈን ገንዘብ አግኝተናል

8. መተዳደሪያ ደንቡን በመከተል በ2023 4 ቤተሰብ አባላት አድርገን መዝግበናል
9.በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተጨማሪ ስዕል እንዲሰራ ወስነናል

## መ.የጥገና እና እድሳት የዓመታዊ ሪፖርት

የቤተክርስቲያናችን ህንፃ አስፈላጊውን እድሳት እና ጥገና በማድረግ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ሓላፊነቱን ወስዶ በዚህ ባሳለፍነው ዓመት የሚከተሉትን ሥራዎች ተከናውናዋል

1.July 2, 2023- የማዕድ ቤት መብራት በአዲስ LED florecent አንፓል ተቀይሮ ተሰርቷል
2.October 29, 2023- የአደራሹን መብራት በአዲስ LED florecent አንፓል ተቀይሮ ተሰርቷል
3.December 10, 2023 - የምድር ቤት ሁለት የወንዶች እና የሴቶች መፀዳጃ
(ሽንት ቤት )መቀመጫ ለሁለቱም አዲስ ተገዝቶ ተቀይሯል
4.December 24, 2023 - የቤተ ክርስቲያን ዋናው በር እና አንድ የደጅ መብራት ጥገና ተደርጓል

## ሠ.2023 የዕቅድና ልማት (የፋይናንስ) ኮሚቴ ሪፖርት

የእቅድና ልማት ኮሚቴ አባላት ወ/ሮ ትእግስት ዘገዬ፣ ወ/ሮ ደብሪቱ ለማ እና ወ/ሮ ስብለወንጌል መሰረት ናቸው።

በ 2023 ገንዘብ ማሰባሰብ የተደረገው በአራት (4) መንገዶች በኩል ነው። እነዚህም፡-

1) የኢትዮጵያን አዲስ አመት በአል አስመልክቶ
2) በፊላደልፊያና እና አካባቢው በተደረገው የኢትዮጵያውያን ቀን (Ethiopian's Day)
3) በ Giving Tuesday (ጊቪንግ ቲውስዴይ) እና
4) በንዋየ ቅድሳት ሽያጭ

በ 9/9/23 ለቤተ ክርስቲያናችን ገቢ ማሰባሰቢያ የPicnic ዝግጅት ተደርጓል። እንደምታስታውሱት፣ በሁላችሁም ትብብር ዝግጅታችን በአማረ ሁኔታ ካሰብነው በላይ ውጤታማ ሆኖልናል። በዚህ ዝግጅት $4,223.00 ለቤተክርስቲያን ገብቷል።

በ 9/30/23 ቤተክርስቲያናችን በ ኢትዮጵያን ዴይ ፕላኒንግ ኮሚቴ (Ethiopian's Day Planning Committee) እንደተሳተፈችና በዕለቱ ካህናትና ምእመናን በተገኙበት በደመቀ ሁኔታ እንዳከበርን ይታወሳል። በእለቱ ቀን ከልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ሽያጭ $911.00 ለቤተክርስቲያናችን ገብቷል።

በአቶ ኤፍሬም ካባ አደራጅነት በ Giving Tuesday (ጊቪንግ ቲውስዴይ) ለቤተክርስቲያናችን አስራሁለት (12) ስእሎችን ከኢትዮጵያ አስሎ ለማስመጣት በተደረገው ውሳኔ $5,701 ገቢ ተደርጓል።

የእቅድና ልማት ኮሚቴ አባሎች እና የቤተክርስቲያን ምእመናን ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን ለሽያጭ አቅርበዋል። በ 2023 የነዋይ ቅድሳት ሽያጭ $4,303 ገቢ ሆኗል።

በአጠቃላይ በ 2023 የእቅድና ልማት ኮሚቴ $15,138 ለቤተክርስቲያናችን ማስገባቱን ሲገልጽ በታላቅ አክብሮት ሲሆን እንዲሁም በቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ስም እግዚአብሄር ይስጥልን በማለት ምስጋና ያቀርባል።

## ረ.የቤተክርስቲያን የህግ ጉዳይ ሪፖርት

እንደሚታወቀው የሰበካ ጉባኤው ልዩ ኮሚቴ አቋቁሞ ህጉን እንዲከታተል አድርጓል። የህግ ኮሚቴ አባሎች ወ/ሮ ትእግስት ዘገዬ እና ወ/ሮ ሄርሜላ አባተ ሲሆኑ በተጨማሪም አቶ ኤፍሬም ካባ እና ዶ/ር ቅጣው ነጋሽ አብረው ያገለግላሉ።

በድሮ አማኑኤል ቤተክርስቲያን የህግ ጉዳይ በተመለከተ ለጠበቃው ይህ ቤተክርስቲያን ጉዳዩ እንደማይመለከተው በኢሜል እና በሬጅስተርድ ደብዳቤ አስታውቀናል።

ወስብሀት ለእግዚአብሔር